
# ጮክ ብሎ የማንበብ መምሪያ ለቤተሰቦች

Reading Is Fundamental.
until every child reads




**ዘ ላይብራሪስ ሰክሪት (The Library's Secret/El secreto de la biblioteca)**
*ደራሲ፤ አና ጋላን (Ana Galan)*
*ሰዓሊ፤ ሮድሪጎ ሉጃን (Rodrigo Lujan)*

**ይዘቶች (Themes)፤** ምናባዊ (Imagination)፤ ተዓምር (Magic)፤ ቤተ-መጻህፍት (Libraries)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤** አንድ ወጣት ልጅ ቤተ መፃህፍቱ አስደናቂ ሚስጥር እንደያዘ ያወቀበት አስማታዊ ጀብዱ፤ መፅሃፍቶች በህይወት ሊኖሩ ይችላሉ!

## ጮክ ብለው ያንብቡ

### ከንባብ በፊት፤ ዳራ ይገንቡ (Build Background)

- ወደ ቤተ-መጽሐፍት ስትሄድ የምትወደው ነገር ምንድን ነው? እዚያ አስደናቂ ነገር ሊከሰት እንደሚችል አስበህ ታውቃለህ?" በማለት ይጠይቁ።
- ይህ ታሪክ በቤተ መፃህፍቱ ውስጥ የማይታመን ነገር ስላወቀ ወንድ ልጅ እንደሆነ ለልጅዎ ያስረዱት። ሲያነቡ፣ ቤተ መፃህፍት ልዩ ቦታዎች ስለሚያደርጋቸው ነገሮች አስቡ።

### በንባብ ወቅት፤ ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

- ልጁ ሌሊት ቤተመፃህፍት ውስጥ ሲቆይ ምን አገኘ?
- አንባቢዎቹ (bookworms) እነማን ናቸው? ቤተ-መጻህፍት ውስጥ ምን ያደርጋሉ?
- ልጁ በቤተመጻሕፍት ውስጥ ስላየው ነገር ምን የተሰማው ይመስልሃል?

### ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ

- "የቤተ-መጻህፍቱ ምስጢር ምንድነው? አንባቢዎች ቤተ-መጻህፍቱን ለመንከባከብ የሚረዱት ለምን ይመስልሃል?" በማለት ይጠይቁ።
- መፅሃፎች በህይወት ቢኖሩ የትኛውን መጽሐፍ መመርመር ትፈልጋለህ? ለምን?" በማለት ይጠይቁ።

## ተዛማጅ ተግባራት

### ልጅዎ ይህንን መጽሃፍ ከወደደው፤

- "ለሊትን በቤተ-መጻህፍት (Night at the Library)" ስእል ይፍጠሩ። ልጅዎ በቤተ-መጻህፍት ውስጥ አንድ ሌሊት እንደሚቆይ እንዲያስብ ያድርጉት። ምን ያይ ይሆን? መጽሃፍቶች በህይወት ሲመጡ ወይም አንባቢዎች (bookworms) ስራቸውን ሲሰሩ ይሳሉ።


©2026 Reading Is Fundamental